## ከጁላይ 11-20 የነበርው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በምዕራብ አጋማሽ እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ የተስተዋለ ሲሆን፤ አልፎ አልፎም በተዳከመ ሁኔታም ቢሆን ወደ ደቡብ፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይም ተስፋፍቶ ተስተዉሏል፡፡

በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከተፈጠረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ እስከ 121.6 በሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ሁኔታ ለግብርና ስራ እንቅስቃሴና ለውሀ ሀብት ጠቀሜታው የጎላ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

## ከጁላይ 21-31 የሚጠበቀው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

ባለፉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ተጠናክረው በመቆየታቸው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎች ላይ ከሞላ ጎደል በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሰፋፉ ዝናብ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በተለያዩ ሀገሪቱ ሥፍራዎች ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረውና ከዚሁም ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት የጁላይ መጨረሳቹ አስር ቀናት የሚኖረው ዝናብ ለእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ለውሀው ዘርፍ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

# <u>ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2018 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>


በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሁለተኛዉ አሥር ቀናት የወቅቱ ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በይበልጥ የሚጠናከሩበትና የዝናቡ ስርጭትም አብዛኛዉ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚያዳርስ ሲሆን፤ በመጠንም ረገድ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የሚመዘገብበት ጊዜ ነዉ፡፡

ባለፉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በምዕራብ አጋማሽ እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ የተስተዋለ ሲሆን፤ አልፎ አልፎም በተዳከመ ሁኔታም ቢሆን ወደ ደቡብ፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይም ተስፋፍቶ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከተፈጠረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ እስከ 121.6 በሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጠቀስ ያህል በሶኔ 121.6፣ በአርሲ ሮቤ 46.4፣ በአለም ከተማ 49.8፣ በአቦምሳ 32.4፣ በአርጆ 42.8፣ በአምባ ማሪያም 40.9፣ በአይደር 46፣ በአዋሽ አርባ 48.0፣ በባህርዳር 32.2፣ በባቲ 64.2፣ በቡኢ 36.0፣ በቡለን 30.7፣ በጨፋ 30.8፣ በደብረ ብርሃን 33.3፣ በደብረ ታቦር 30.6፣ በኢጃጂ 98.1፣ በፍቼ 36.2፣ በጊምቢ 50.5፣ በካቺስ 44.0 እና 34.1፣ በላሊበላ 34.9፣ በሊሙ ገነት 32.0፣ በማጀቴ 44.5፣ በማንኩሽ 49.0፣ በሚኤሶ 37.1፣ በአዳማ 43.1፣ በነጆ 37.0፣ በነቀምቴ 42.2፣ በሰኮሩ 34.2፣ በሽሬ 36.8፣ በሽራሮ 79.6፣ በወረኢሉ 49.9 እና 47.9፣ በወሊሶ 49.4 እና 42.4፣ በአማን 44.4፣ በቴፒ 36.5፣ በጊዳ አያና 48.4 እና በጉንዶ መስቀል 43.3 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ ዝናብ ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በመካከለኛዉ፣ በደቡብ እና ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፤ በሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ በዋግህምራ ዞን፤ ከሞላ ጎደል በሁሉም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፤ በሁሉም የወለጋ እና የሸዋ ዞኖች፣ በኢሉአባቦራ፣ በጅማ፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በከፋ እና በሸካ ዞኖች፣ በወላይታ፣ በጋሞጎፋ፣ በጌዴኦ እና ሲዳማ ዞኖች፤ በአፋር ክልል ዞን 01፣ 03 እና 05 ከ 25-205 በሚ.ሜ ለ2-8 ቀናት ያህል የዘነበ ሲሆን፤ በአንዳንድ የአርሲ እና ባሌ፣ ጉጂ እና ቦረና፣ በደቡብ ኦሞ እና ሰገን ህዝቦች ላይም ከ5-25 በሚ.ሜ ለ1-5 ቀናት ያህል ዘንቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር የምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ፣ የአማራ ክልል ምስራቃዊ ክፍል፣ ጥቂት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፣ ምዕራብ እና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ የጋምቤላ እና የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ምዕራባዊ ክፍል፣ አብዛኛዉ የአፋር ክልል ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡

ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2   ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት



**ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር**







በወቅቱ ዝናብ የማያገኙ አካባቢዎች | ከመደበኛ በታች | መደበኛ | ከመደበኛ በላይ

# <u>እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

ባለፉት የጁላይ ሁለተኛው አስር ቀናት የወቅቱ የክረምት ዝናብ በአብዛኛው በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ የቀጠለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ ጥሩ ዝናብ ከማግኘታቸው ጋር ተያይዞ የተሻለ የአፈር እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በወቅቱ ለሚከናወኑ የመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ በተለይም፣ ለዘር መዝራትና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ስብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። በተጨማሪም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አከባቢዎች ለመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለግጦሽ ሳር ልምላሜ የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በሌላም በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በተወሰነ መልኩ በግብርናው ሥራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ አካባቢዎች ነፋስና በረዶ ቀላቅሎ የጣለዉ ከባድ ዝናብ (በፅጊቃ እና በጊዳአያና ) በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ እንዲሁም በረዶ ቀላቅሎ የጣለዉ ከባድ ዝናብ በአንዳንድ ሥፍራዎች በእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች እና ቋሚ ተክሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረዉ (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከ11-20 ጁላይ 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በሀገሪቱ ምዕራባዊ አጋማሽ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የተስተዋለ ሲሆን፤ በላይኛው ባሮአኮቦና ኦሞጊቤ እንዲሁም በአብዛኛው የአባይ ታፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት ተስተውሏል$ ከዚህ ጋር ተያይዞ አብዛኛው ባሮአኮቦ" ተከዜ የላይኛው ኦሞጊቤ" የመካከለኛውና የላይኛው አዋሽ" የላይኛው ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም የላይኛው አፋርደናከል ተፋሰሶች የተሻለ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው$ በሌላ በኩል አብዛኛው ዋቢሸበሌና ገናሌዳዋ" የአፋርደናከል ምስራቃዊው ክፍል" የታችኛው አዋሽ" የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆና ኦሞጊቤ ተፋሰሶች በአብዛኛው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ የተስተዋለባቸው ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል$ በመሆኑም ባለፉት አስር ቀናት የተገኘው እርጥበት ለውሃ ፍላጎት ግብዓት አስተዋፆ ከማድረጉም በላይ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ በመኖሩ የወንዞች ሙላት እና በረባዳ ቦታዎች ላይ ውሃ መተኛት ተከስ~ል (ካርታ 5)።

ካርታ 5   እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

ባለፉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ተጠናክረው በመቆየታቸው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎች ላይ ከሞላ ጎደል በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሰፋፉ ዝናብ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ። በተመሳሳይ መልኩም በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረውና ከዚሁም ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የሰሜን ሸዋ በተጨማሪም የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ሁሉም የትግራይ ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የጉራጌ፣ የሀዲያ፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋና የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት መንስኤ ሊሆን ይችላል። ከዚህም ሌላ ድሬዳዋና ሐረሪ የአፋር ዞን 3፣4 እና 5፤ የአርሲና ባሌ ዞኖች፣ እንዲሁም የጅጅጋና የሽንሌ ዞኖች አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት መጠነኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ከላይ በተሰጠው ትንበያ መሠረት በሚቀጥሉት የጁላይ ሶስተኛው አሥር ቀናት በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረውና ከዚሁም ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ጥሩ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸውና በተለይም የክረምት ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ይበልጥ የተጠናከረ ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ ለግብርናው ስራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉና፣ አስቀድመው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የሚገኘዉ እርጥበት በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የመኸር ወቅት እርሻ እንቅስቃሴን ዘግይተው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበትን የሚያሻሽል ሲሆንና የመኸር ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት ምቹ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እና በአሁን ጊዜ እርጥበት በማግኘት ላይ ለሚገኙት በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል። በሌላም በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት በተለይም በተከታታይ ዝናብ እያገኙ ባሉ አካባቢዎች ላይ ዉሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማዉጣትና የማንጣፈፍ ስራ በመስራት፣ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ላሉ ሰብሎች አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረው ተገቢዉን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ከእርጥበት መብዛትና በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት ጋር የፀረ ሰብል ተባይና  የአረም መከሰት ሊኖር ሰለሚችል የሚመለከተው ክፍል በየጊዜው የማሳ ጉብኝት በማድረግ ጥንቃቄ እንዲወስድ እንመክራለን፡፡

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

የክረምቱ ዝናብ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ በተጠናከረ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በሚያገኙት ተፋሰሶች ላይ ቀጣይነት እንዳለው ትንበያው ያመለክታል፡፡ ይህንን ተከትሎ የአባይ፣ አብዛኛው የተከዜ፣ የባሮአኮቦ፣ የላይኛውና የመካከለኛው የኦሞጊቤ፣ የአዋሽና የስምጥሸለቆ እንዲሁም የላይኛው አፋር ደናከል ተፋሰሶች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ በእነዚህ ተፋሰሶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ትንበያው ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም የላይኛውና መካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ እንዲሁም የታችኛው ኦሞጊቤ ተፋሰሶች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህ ሁኔታ ለውሃ ሃብት መጠን መጨመር ጥሩ አስተዋፆ ቢኖረውም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚከሰተው ከባድ ዝናብ በገደላማ ቦታዎች ላይ መሬት መንሸራተትና እንዲሁም  የወንዞች ሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች ላይ ደግሞ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል ጥንቃቅ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡